1ኛ ዓመት ቁጥር 17
1st Year No. 17

ባሕር ዳር ጥር 22 /1989 ዓ.ም. Bahir Dar 30th date of Feb. 1997

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P.O.BOX

ማ ው ጫ	CONTENTS
አዋጅ ቁጥር 17/1989 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሸጋሸግ የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ገጽ 3	Proclamation No-17/1997 A Proclamation to Amend the Proclamation that Provides for the Reallotement of the possession of Rural land in the Amhara National Region. Page 3

አዋጅ ቁጥር 17/1989 ዓ.ም የአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሸጋሸግ የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሸጋሸግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 16/1989 ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሸጋሸግ የወጣውን አዋጅ ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 17/1989 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Proclamation No-17/1997 A Proclamation to Amend the Proclamation that Provides for the Reallotement of the possession of Rural land in the Amhara National Region

Where as, it has become necessary to amend proclamation number 16/1997 that provides for the reallotment of the possession of rural land in the Amhara National Region;

Now therefore, in accordance with sub article 3(1) of article 49 of the constitution the council of the Amhara National Regional State here by proclamed as follows.

1. Short Title

This proclamation may be cited as "an amendment of the proclamation that provides for the reallotment of the possession of rural land in the Amhara National Region. No 17/1997"

2. ማሻሻያ

በአማራ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት ይዞታን ለማሻሻያ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 16/1989 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. በአንቀጽ 2 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 8 ከተዘረዘሩት ትርጓሜዎች በተጨማሪ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 9 ታክሏል።

   9. «የገጠር ቀበሌ» ማለት ለኢኮኖሚያዊ፣ ለአስተዳደራዊና ለማህበራዊ ጠቀሜታቸው ሲባል በአዲስ መልክ የተደራጁትን ወይም በአዲስ መልክ የማደራጁቱ ስራ ከመሰራቱ በፊት የነበሩትን የቀበሌ ክልሎች ነው።

2. አየንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

   1. ይልጻይ ኮሚቴው የክልሉ መስተዳድር በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ መሠረት ከአጣሪ ኮሚቴው የተረከበውን የነዋሪ ሕዝብ ብዛትና የመሬት ይዞታ ሰነድ ተመልክቶ ለየአንዳንዱ ቤተሰብ የሚደርሰውን የመሬት ይዞታ መጠን ይወስናል።

3. በአንቀጽ 18 ርዕስ ስር የሰፈሩት ንአንቀፆች ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንአንቀፆች ተተክተዋል።

   18. የመሬት ይዞታ ይልጻይ ኮሚቴ አወቃቀር

   1. በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ክልል ውስጥ በነዋሪው ሕዝብ የሚመረጥ ተጠሪነቱ ለመረጠው ሕዝብና ለቀበሌው መስተዳድር የሆነ የመሬት ይዞታ ይልጻይ ኮሚቴ ይቋቋማል።

   2. ኮሚቴው በንዑስ ኮሚቴዎች ተደራጅቶ ሊሰራ ይችላል።

   3. የኮሚቴው አባላት አመራረጥ የሚኖሩትን ጎጦች ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ ቁጥሩ እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን ይሆናል።

   4. ኮሚቴውም ሆነ ንዑስ ኮሚቴው አንድ ሊቀመንበርና ፀሐፊ ይኖሩዋቸዋል።

4. አንቀጽ 21 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

   1. በእጣ አወጣጥና ድልድል ተግባር በደል ተፈጽሞብኛል የሚል ማንኛውም የቀበሌ ነዋሪ ይልጻይ ኮሚቴው ሥራውን ባጠናቀቀ እስከ አንድ ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል።

5. የአንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል።

   2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 ስር በተደነገገው መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ኬሉገር

2. Amendment

Proclamation No 16/1997 that provides for the reallotment of possession of rural land in the Amhara National Region is amended as follows.

1. Besides the definitions provided from sub article 1 to 8 of article 2, the following new article 9 is here by added.

   9 " Rural Kebele" means those kebele areas, oraganized in a new manner for their economic administrative and social benefits, or, the kebeles existing before the task of organizing the same was performed.

2. Sub article 1 of article 7 is here by deleted and replaced by the following new sub article 1

   1. The reallotting committee, pursuant to the regulation or directive to be issued by the regional state shall determine the size of land possession to be allotted to each family by referring to the document it received from the verifying committee which contains the number of the inhabitants and the size of land;

3. The sub article provided under the title of article 18 are here by deleted and replaced by the following new sub articles.

   18. Organization of the land possession Reallotting Committee

   1. In the locality of each rural kebele areas, a land possession reallotting committee, nominated by the inhabitants and accountable to the nominee and the kebele administration shall be established;
   2. The committee may function, by being organized in sub committees.
   3. The nomination of the members of the committee; and their numbers shall be determined as may be necessary, taking the existing individual villages in to account.
   4. The committee as well as the sub committee shall have a chairman and secretary.

4. Sub article 1 of article 21 is here by deleted and replaced by the following new sub article 1.

   1. Any inhabitants of the respective kebele who claims that, he is mistreated in the process of casting a lot and reallotting activities may submit his/her pettion to the grievance hearing committee with in a period of a week right after the committee has completed its reallotting activity.

5. Sub article 2 of article 22 is here by deleted and replaced by the following new sub article 2.

   2. The grievance hearing committee to be established persuant to the provision of sub article 1 of this

157

ሽማግሌዎች እና ከቀበሌው መስተዳድር የተውጣጡ አባላትን የሚይዝ የሆናል።

6. አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል። በተጨማሪም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 7 ታክሏል።
   2. የመሬት ድልድሉ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ ሦስት ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ የቀረቡለትን ቅሬታዎች መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።
   7. የክልል መስተዳድሩ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
7. የአንቀጽ 24 ድንጋጌ በሙሉ ተሰርዞ በሚከተለው ድንጋጌ ተተክቷል።
   24. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚመለከታቸው ዝርዝር ጉዳዮች የክልል መስተዳድሩ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ይወሰናል።
8. የአንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ተሰርዘው የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ተተክተዋል።
   3. የመሬት ሽግሽጉ በሚካሄድባቸው ቦታዎች በቀበሌው ፍትህ ኮሚቴ ወይም በመደበኛ ፍ/ቤት የተያዙ ማንኛውም የገጠር መሬት ይዞታን የተመለከቱ ክርክሮች በሙሉ አይታዩም።
   4. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሬት ሽግሽጉ ሒደት ላይ የመሬት ይዞታቸው በመቀነስ ወይም በመጨመር የመሬት ይዞታ ለውጥ ያልተደረገባቸውን መሬቶች የሚከሉት ነባር የይዞታ ክርክሮች ከመሬት ሽግሽጉ መጠናቀቅ በኋላ ጉዳዮች በተያዘባቸው አካላት መታየት ይቀጥላሉ።
9. በአንቀጽ 29 ያመለክሰስ መብትን የማመለከት አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተጨምሮ ሌሎች ተከታታይ አንቀፆች በቅደም ተከተላቸው መሠረት ተስተካክለዋል።
   29. ያለመከሰስ መብት
   ማንኛውም የመሬት ደልዳይ ኮሚቴ አባል የመሬት ድልድሉን ሥራ እስከሚያጠናቅቅበት ወቅት ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለወረዳው መስተዳድር ፈቃድ አይያዝም፣ አይከሰስም።

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

በሕር ዳር
ጥር 22 /1989 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

article shall have members consisting from elder inhabitnts and the kebele administration.

6. Sub article 2 of article 23 is here by deleted and replaced by new sub article 2 and in addition the following new sub article 7 is added.
   2. Render its decision with in a perid of three weeks, up on complaints submitted to it, after the reallotting activities have been completed.
   7. Perform such other duties, as assigned to it, by the regional administration.
7. The provision of article 24 is here by deleted and replaced by the following new provision.
   24. The details of matters to be entertained, by the grievnce hearing committee shall be determined by regulation or directive to be issued by the regional administration.
8. Sub article 2 and 3 of article 28 are here by deleted and replaced by the following new sub article 2 and 3.
   2. Any cases, involving rural land possession pending in the kebele justice committee or ordinary court of the areas where land reallotment is to be carried out, shall not be entertained.
   3. Without prejudice to sub article 2 of this article, former suites involving possessions of those lands which are not affected in size either by increament or decreament in the process of the reallotment, shall be entertained by the bodies pending them after the completion of the same.
9. Under article 29 a new article concerning the right of immunity added and there by the consecutive article are adjusted in accordance with their sequential order.
   29. Right of Immunity
   No members of the reallotting committee may be caught or prosecuted with out the permission of the woreda administration except when caught in flagrant delicto until he completes land reallotting activities.

3. <u>Effective Date</u>

This regulation shall enter in to force on the date of its retification by the council of the Amhara National Regional State.

Done at Bahir Dar
30th date of Feb. 1997
The Council of the Amhara National Regional State

158